# የመጨረሻው ሰይጣን
## ክፍል 8

አዲስ አባባ ካለፈው የቀጠለ
ከበልጅግ አሊ

በተለይ ከሰው ጠባይ ጋር መግባባት አልቻልኩም ። በተለይ አንዳንዱ ሰው ሰላም ስትለው እንደሞኝ ነው የሚቆጥርህ በኋላ እኔም እራሴ ሁሉንም ሰላም ማለት አቆምኩ ። በአነጋገሬ ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ ይስቁብኝ ነበር ። ምንም እንኳን ምን እንደሚያስቃቸው ሁኔታው ባይገባኝም እኔ ግን ከመናገር ተቆጠብኩ ። የአባቴ ሁኔታ ደግሞ ህልሜም በውኔም እየመጣ እረፍት ነሳኝ ። ሁል ጊዜ አስከሬኑ ይታየኛል ። ሁል ግዜ የተቆረጠው ምላሱ ትዝ ይለኛል።ይሄ ሲታሰበኝ ሰው ያስጠላኛልና ዝምታን እመርጣለሁ። አንድ ጊዜ ትምህርት ቤት ከአንድ ልጅ ጋር ተጣላንና ጭቅጭቁ ወደ ድብድብ አመራ። ልጁን ለመታው ስጠጋው የአባቴ እሬሳ በሃሳቤ መጣ ። ልጁም የአባቴ ገዳይ መሰለኝ። አይኖቼን አጉረጥርጬ በጣም እደበድበው ጀመር። ለኔ ለራሴ ሌላ ሰው የሆንኩ መሰለኝ። ይህን አይነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም። ከዛ ሰዎች ደርሰው ባይገላግሉኝ ኖሮ ልጁን ገድዬው ነበር። ከዛ በኋላ ትምህርት ቤት ውሰጥ ሁሉም ይፈሩኝና ይሸሹኝ ጀመር። ያም እኔ ሰውን እንድጠላ አደረገኝ። ተማሪዎቹ የፍርሃት ይሁን የማክበር ሁሉንም ለኔ ይለቁልኝ ጀመር። የምፈልገው ጠይቄ ማንም እንቢ አይለኝም ። በአንድ በኩል አዲሱ ያገኘሁትን ክብር ስወደው በአንድ በኩል ደግሞ የጓደኞቼ ከእኔ መራቅ ሰው እንድጠላ አደረገኝ። የአባቴን ገዳዮች አንድ ቀን ለፍርድ ማቅረብ እንዳለብኝ ሁልቀን ይሰማኝ ነበር። እነርሱን ለመግደልና ደም ለመመለስ አልፈልግም ነበር። ምክንያቱም እኔ የአባቴ አይነት እጣ ይደርሰኛል ብዬ እፈራ ነበር። ከዛ ሁሉ በህግ ቢታሰሩ ሞት ወይም እድሜ ልክ ስለሚፈረድባቸው አንድም እኔ የምፈራው ነገር አይሆንም ፣ ሁለተኛ ደግሞ በቀጥታ እኔ እንደሆንኩ ወደ ፍርድ ቤት ያቀረብኩዋቸው አያውቁም ብዬ አስብ ነበር። መጀመሪያ አካባቢ አዲስ አበባ መጥተው ይገሉኛል ብዬ የምፈራው እና ሁሉን በጥርጣሬ የማየው እየቆየሁ ስመጣ እየጠፉ መጣ።

የአጉቴ ቤት በጣም የሚስማማ ነው። የአጎቴም ሚሰት የሚች ልጅ ነው ብላ በጣም ነበር የምትንከባከበኝ። አንዳንዴ እሷ በጣም ስትቆጣ ለኔ ቁጣም አይመስለኝም ነበር። እኔም በበኩሌ እሷ የምታዘኝን ሁሉ ለመፈፀም ጥረት አደርጋለሁ። የመታዘኝም ከባድ ስላልሆነ ለመስራት ፈቀደኛ ነኝ። ከባዱ ስራ የታጠበውን አንሶላ ወይም ጋቢ ጨምቆ ማስጣት ነው። አንድ ቀን ሰው ስለጠፋ እህል አስፈጭ ብላ ብትልከኝ ስመለስ አጎቴ አይቶ እዚህ የመጣው ሊማር እንጂ እህል ሊያስፈጭ አደለም ብሎ ተቆጣ። አጎቴ ያልገባው ነገር ቢኖር እህል ማስፈጨቱ የሕፃንነቴን ጊዜ ስለሚያስታውሰኝና የእህሉን ሽታ ስለምወደው ብዙ ጊዜ ብሄድ ደስ እንደሚለኝ ነው። ከዛም ውጭ ከየቤቱ የመጡ ሰራተኞች ተሰብስበን ተራችን እስከሚደርስ ስለመጣንበት አገር ስለምናወራ በጣም ደስ ይለኝ ነበር። በአነጋገርም በችግርም እኔን የመሰሉ ሰዎች ስለማገኝ ደስታዬ ወሰን አልነበረውም። ቢሆንም አጎቴ ሲቆጣ ምንም አላልኩም። በኋላ ግን ለአጎቴ ሚስት ስነግራት እሷም አይሆንም መሄድህን ከአወቀ ይገለኛል አለችኝ።

መጀመሪያ አካባቢ አልጋ ላይ መተኛት ይከብደኝ ነበር። እገጠር እያለሁ መደብ ላይ ነው ሰለምተኛና ንፅህናው እንብዛ ስለነበር ነጭ አንሶላ ላይ መተኛት እንዴት እጠላ እንደነበር ሳስታውስ ሳቄ ይመጣል ። የከተማው ምግብ አንዳንዴ በጣም ነው የሚገርመኝ። ለመብላት የሚያስቸግር ሁሉ አለበት ። እኔ በማንኪያና ሹካ በልቼ አላውቅም። አጎቴ ደግሞ የተማረ ስለነበር ለእርሱ የውጭ ምግብ በጣም ይስማማው ስለነበር ሁልግዜ ፓስታ ፣መኮረኒ ሲሰራ መብላት ይጨንቀኝ ጀመር ። አጎቴ ይህንን

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አውቆ እንዴት እንደሚበላ ቢያስተምረኝም ስላልጣመኝ ፓስታም ይሁን መኮሮኒ በእንጃራ ነው የምበላው። አንድ ቀን አጎቴ ፓስታ በእንጀራ ስበላ እኔ ከምበላው ቀመሰና እንደሚጣፍጥ ሲገባው ከዛ በኋላ ሁል ጊዜ ፓስታ በእንጀራ ነው የሚበላው ። አጎቴም

- ስማ ይግረም እንዴት ጥሩ ነገር አስተማርከኝ እባክህ ?
- አጎቴ ቢቸግረኝ እኮ ነው በሹካ መጠቅለሉን ስላልቻልኩበት እኮ ነው እንደዚህ የምበላው ።
- ይገባኛል ይህ እኮ ጥሩ ምሳሌ ነው ። በእኛ አገር የሚገኘውን ከፈረንጁ ጋር ብናደባልቀው እንዴት ጥሩ እንደሆነ አየሽው።ይህ በሁሉም ቦታ ሊለመድ ይገባል። በተለይ በእርሻ ላይ ይህን ካልተጠቀምን ውጤቱ አያምርም። ለዚህ ነው ገበሬው ለፍቶ ሰርቶ ውጤቱ የማያምረው። ያ ሁሉ ጉልበት ወጥቶ የሚገባው ትንሽ ነው። ምን ለአንተ እነግርሃለሁ ታውቀው የለ።
- አውቀዋለሁ ። ግን ህዝቡ የሚቀበለው አይመስለኝም ። አዲስ ነገር ስለሆነ መቼም ስም ያወጡለታል።
- ማስተማር ያስፈልጋል። ሰርቶ ማሳየት። በማስገደድ አይሆንም።
- እሱማ መች አጥቼው ባህል አለ፣ ሃይማኖት አለ፣ ብዙ ብዙ ነገር አለ። ባለፈው እኛ አገር የተመደበው የግብርና ሰራተኛ በመደዳ በቆሎውን ዝሩ ብሎ አዞ ነበር ።ታዲያ ያገሩ ሰው ጥሬ ስንቆጥር እንውልም ብሎ እንቢ አለ። መቼም በመበተን መዝራት ቀላል ቢሆንም ውጤቱ ግ አነስተኛ ነው። ለስራም ከባድ ነው አልኩት።

አጎቴ እንዳንድ ጉዳይ ሲያጫውተኝ በጣም ነበር ደስ የሚለኝ። አባቴ አጎቴን ለምን እንደሚወደው አሁን ነው የገባኝ። ሚስቱን በጣም ነው የሚከብራት እሷም እንዲሁ። እዚህ ቤት እንኳ በበርበሬ ልጅን ማጠን ስድብ እንኳ አይሰማም። አጎቴ ስለ አባቴ እኔ ፊት ማንሳት አይወድም፣ ሰዎች እንኳ ካነሱ ቶሎ ብሎ አርዕስቱን ይቀይራል ። በጣም ከፍተኛ አዘንም ከፊቱ ይነበባል ።አንድ ቀን አጎቴን እንዴት እዚህ እንደደረሰ ጠየቅሁት።

ስማ ይግረም የኔ ህይወት በጣም ከባድ ነው። ገና በልጅነቴ እረኛ ነበርኩ። ምን አልባት እኔ እራሴ የምጠበቅበት ጊዜ ነበር። በዛ ግዜ ነው አላፊነት መሸከም የጀመርኩት። ከብቶቹን መጠበቅ ነበረብኝ። አንድ ቀን ቀበሮ መጣና በጣም አስደነገጠኝ። አንድ በግም ገደለብኝ ። በጣም ፍርሃት ዋጠኝ። ለማንም ሳልነግር ወደ ከተማ ሄድኩ። ብመለስ የሚደርስብኝን ሳስበው አሁንም ይዘገንነኛል። ግርፉ ቁጣው እንኳን አጥፍቼ ያጠፋል ተብሎ ከተገመተ አይቀርልኝም ነበር። ወደ ከተማ ስሄድ ምን እንደሚገጥመኝ ወይም ምን እንደምፈልግ አላውቅም። አንድ የማውቀው ነገር ቢኖር አንድ አክስታችን አዲስ አበባ ትኖራለችን የሚል ነበር። የት እንደምትኖር አላውቅም ነበር። ከተማ እንደገባሁ አዲስ አባባ ለመሄድ የተነሳ መኪና ለምኜ ወደ አዲስ አበባ አመጣኝ። አዲስ አበባ አሁን እንደምታየው ትልቅ አልነበረም። ሰዉም እንዲህ እንደ አሁኑ በጣም የሰለጠን አልነበረም። ቤተክርስትያን ተጠግቼ ምግቤን እየለምንኩ ቄስ ትምህርት ቤት መማር ጀመርኩ። ትምህርት ቤት መሄድ ትምህርት ቤቱ የካቶሊክ ነው እየተባለ ከባድ ነበር ቢሆንም ለኔ ጥሩ ሆነልኝ፣ ትምህርት ለመማር ቻልኩ።

ትምህርት መማር በጣም ቀላል አልነበረም፣ ግን ቢሆንም በትግል መማር ቻልኩ። በትምህርት እየገፋሁ ስመጣ ትንሽ ስራ እየሰራሁ ገንዘብ ማሰባሰብ ቻልኩ። ቤተሰቦቼ ሞቶአል ብለው ተሰፋ ቆርጠው ነበር። ትንሽ ገንዘብ ከያዝኩ በኃላ እነርሱን በተለይም እናቴን ለመጠየቅ ፍላጎት አደረብኝ። ተነስቼ ወደ ቤት ብመለስ አባቴ ሞቶ እናቴ በኔ ሃዘን ተጎሳቁላ ደረስኩኝ። ማንም ያመነ አልነበረም ። ደስታም ለቅሶም አንድ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ላይ ሆነ። ትንሽ ቀን እንደቆየሁ ለመመለስ መፈለጌን ተናገርኩ። አባትህ ከእኔ ጋር ለመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት አደረበት ቢሆንም እናታችን ብቻዋን ትሆናለች ብለን እንዲቆይ ተስማማን። አባትህ ለኔ በጣም ፍቅር ነበረው። በጣምም እንግባባም ነበር። እሱ ከገጠር ሁሉን ነገር ሲልክልኝ እኔም ከዚህ የተቻለኝን አደርግለት ነበር። መቸም ብዙ ችግር ደርሶበታል። ብዙም ተሰቃይቶአል። ሰዎች እሱን አይረዱትም እንጂ በጣም እሩህሩህ ሰው ነበረ። እዚህ መጥቶ ቢማር ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን በመጀመሪያ የእናታችን ጉዳይ ከዛም የኔ እራሴን አለመቻል እንዳይመጣ አደረገው። በዛም ነው እንደዚያ ያለ ችግር ውስጥ የገባው። ሁኔታውን ስሰማ በጣም ነበር ያዘንኩት ግን ምንም ማድርግ ስላልቻልኩ እዛው እንዲታረቅ ትልቅ ጥረት አደረግኩኝ። የተከፈለው ተከፈለ እሱም ወደ ቤቱ በሰላም ወደ ቤቱ ተመለሰ። አሁን ግዜው አልፎ ሁሉ በተረሳበት ግዜ ይህ ሆነ። ግን እንግዲህ አንተን ይህ የሚመለከትህ አደለም። አንተ ትምህርትህ ላይ ነው ትኩረት መስጠት አለብህ። እነርሱም ሆነ እኛ ዘመዶችህ ነን። ስለዚህ ምንም ነገር ማሰብ የለብህም። ገዳዮቹን በህግ እንዲቀጡ ማድረግ ነው እንጂ በግል ምንም እርምጃ መውሰድ የለብንም። ስለዚህ በርታ አለኝ።

እኔም እንኳ በህግ የአባቴን ገዳይ ለመከታተል ብፈልግም ግን እንዴት አደርጌ እንደምጀምር ምንም አላሰብኩበትም ነበር። አጎቴ ለፖሊስ እንዳመለከተና ማመልከቻ እንደፃፈ አውቃለሁ። ነገር ግን ምንም የሆነ ውጤት አልተገኘም። እየቆየሁ ስሄድ ከከተማው ኑሮ እየተስማማሁ የአባቴን ጉዳይ እየረሳሁ መጣሁ። ሆኖም ከልጆች ጋር በምጣላ ጊዜም ሆነ አንዳንዴ በህልሜ የአባቴ ሁኔታ ስለሚታየኝ ሁለመናዬ ይለዋወጥብኛል።

ግዜው እያለፈ መጥቶ አገራችን ውስጥ አብዮት ሲፈነዳ የአጎቴም ንብረት ስለተወሰደ ኑሮ እንደድሮ ሊሆን አልቻልም። የገንዘብ ችግር አጎቴ ላይ ደረሰ። እቤትም ውስጥ ጭቅጭቅ እየበዛ መጣ። እኔ በአንድ በኩል ለደሃው ነው የመጣው በማለት አብዮቱን ብወደውም አጎቴ ስለተጎዳ ደግሞ ሃዘን ገባኝ። ቢሆንም ግን ደስታዬ መጠን አልነበረውም። አጎቴን በግል እረዳዋለሁ ብዬ ስላሰብኩ ሁኔታውን በደስታ ነው የተቀበልኩት። አጎቴም ቢሆን ብዙ የተሰማው አልመሰለኝም ነበር። የአጎቴ ሚስት ግን እኔ መደሰቴን ስታውቅ ለኔ ያላላት አመለካከት ተቀየረ። በዚህ ግዜ ነው ከቤት ለመውጣት ያሰብኩት። ግን የት እንደምሄድ ፣ ምን ስራ መስራት እንደምችል አላውቀውም ነበር። ቢሆንም የአባቴ አገዳዳል የአዕምሮ እረፍት አልሰጠኝም። ገዳዮቹን ለመበቀል በግል እርምጃ መውሰድ  ባልፈልግም አጎቴ እንደመከረኝ በህግ ብጠቀም ግን የሚሻል መሆኑ ቢገባኝም የግዜው መርዘም ደግሞ መረጃዎችንና ምስክሮቹን ማጥፋቱ ይሰማኝ ነበር። አሁን ግን ዋናው ችግሬ የአባቴ ገዳዮች ሳይሆን የእራሴ የመኖርያዬ ቦታ ነው። የአጎቴ ሚስት እንኳን ለኔ ለአጎቴም መቆሚያ መቀመጫ ነው ያሳጣችው። ሁልጊዜ ሲጣሉ እድሏ በአጎቴ ምክንያት እንደተበላሸ ከመናገር አትቆጠብም። በሆነ በአልሆነ የእሷን ቤተሰቦች  ሐብታምነት ተናግራ በውስጠ ታዋቂ የአጎቴን ቤተሰቦች ደሃነት ሳትገልፅ አታልፍም። ትንሽ እየቆየ ሲመጣ ሁኔታው በጣም ስላሳሰበኝ አጎቴን ባነሳበት እሱም ፦

➢ ሁኔታው በጣም አሳሳቢ ነው። የአለኝን ገንዘብ ሁሉ በስተርጅና እጦርበታለሁ ብዬ የከተማ ቦታና በትንሽም ቢሆን የገጠር መሬት ገዛሁበት። እንደምታዬው ለብዙ አመታት የለፋሁበት በአንድ ቀን አዋጅ ተወሰደ። መቼም እኔ ከማንም ወርሼው ወይም ሰርቄው አደለም። ጥሬ ግሬ ነው ያጠራቀምኩት። በዝባዥ አቆርቋዥ ልባልም አይገባም ነበር። የማንንም ገንዘብ ወስጄ አላውቅም። እዚህ ለመድረስ ማንም የረዳኝ የለም።“

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

➢ መቼም ለሃገር ይጠቅማል ካሉ ይሁን ። ግን እኔ አይመስለኝም። አዋጁ ሁሉንም ነው የሚመለከተው አንድም፣ ሁለትም ቤት ያለውንም ወይም ግማሽ አገሩን ያለውንም ባንድ ዓይነት ነው የሚመለከተው። በንደዚህ አይነት ሁኔታ ምንም ወደፊት መስራት አይፈልግም። ከሰራ በኋላ ይወሰድብኛል ብሎ ስለሚያስብ ስራውን ያቆመዋል ። ያ ደግሞ አገርን አያሳድግም። የሆነ ሆኖ ወደ ፊት እናየዋለን።"

➢ አንዳንዴ እሷ ብትናደድ አትፍረድባት። የወደፊት ኑሮአችን ጭለማ እየሆነባት ሲመጣ ጠባይዋ ተለውጥዋል። ቁጣና ብስጭት ታበዛለች። ልጅም የአምላክ ፈቃድ ሆኖ ስላልሰጠን የሚያፅናናት የወደፊቱን በተሰፋ የሚያሳያት ምንም ነገር የለም።

➢ ያኔ መጀመሪያ ስንገናኝ ቤተሰቦቹዋ እኔን እንድታገባ አልፈለጉም ነበር። የሆነ ሆኖ እሷ ካለሱ አልኖርም እራሴን አጠፋለሁ ብላ ታግላ እኔን መርጣ መጣች። በውነት ለመናገር ያለንን ሃብት ሁሉ ወደ መሬት ስለውጠው አልተስማማችም ነበር። ለማንኛውም ትንሽ ጥሬ ገንዘብ እናስቀምጥ ወይም ንግድ እንጀምር ትለኝ ነበር። እኔም ይህ ይመጣል ብዬ ስላላሰብኩ ሁሉንም ወደ መሬት አዋልኩት። ስለዚህ አትፍረድባት ብትናደድ።"

➢ በአንተ በኩል ግን እንደምታየው እንደበፊቱ ብዙ ልንከባከብህ አንችልም። ነገር ግን ባለን ትምህርትህን እንድትቀጥል እንፈልጋለን። ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግህም። ቢቻል ቀን ሰርተህ ማታ የምትማርበት ሁኔታ ቢገኝ ጥሩ ነው። ለአንድንድ ወጭ የሚረዳህን ገንዘብ ታገኛልህ። እንደምታየው አሁን ችግር ላይ ነንና ልንረዳህ አንችልም።

አጎቴ ይህንን ሲነግረኝ እረጋ ብሎ ምንም እንዳልደረሰበት ነበር። ለኔ ያለው ጥንካሬ በጣም ነበር የሚገርመኝ። ሁሉን ነገር እንዳመጣጡ ይቀበለዋል። ነገር ግን በአጠቃላይ የጤንነቱ ጉዳይ የሚያሳስብ ነበር። ደም ብዛትና ስኳር በሽታ ነበረበት። እኔም ጨዋታው ከተነሳ ብዬ ፖሊስነት ለመቀጠር እንዳሰብኩና የአባቴን ገዳዮች ለመከታተል እንዳሰብኩ ነገርኩት። እሱም፦

ያለፈውን ግዜ እርሳው። ለወደፊቱ ግን ተዘጋጅ። የአባትህን ገዳዮች ፈልገህ ለህግ ማቅረብ ማሰብህ ጥሩ ነው። ግን ይህ አገር የስንት ሰው ደም፣ ደመ ከልብ ሆኖ እንደቀረ አትዘንጋ። ብዙ ወንጀሎች ወንጀለኞቹ ሳይገኙ ወይም መርማሪዎቹ በገንዘብ ተገዝተው ወይም ፈርተው ሃቁ ሳይነገር ወይም ሚቾቹ እንደወንጀለኛ ፤ ገዳዮቹ እንደ አልሞት ባይ ተከላካይ ሆነው ሲቀርቡ ስለኖሩ የአንተ አባት ጉዳይ አዲስ እንዳይመስልህ። ነገር ግን አዕምሮህ እረፍት እንዲያገኝ ያ ይሻላል ካልክ ልትቀጥልበት ትችላለህ ። የአንተም አባት ቢሆን እኔና አንተ እንረዳው እንጂ ለሌሎቹ የማይገባ ብዙ ነገር ሰርቶአል። ብዙ የማታውቃቸው ነገሮችን ልትሰማ ስለምትችል ተዘጋጅ አለኝ።

ይቀጥላል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com